## አግሃደት ፍልሰታሃ፡ ማርያም ድንግል!
## በከመ ትንሣኤ ወልዳ፡ ዘልዑል!

## ድንግል ማርያም፡ ፍልሰቷን ገለጠች!
## የልጇን ትንሣኤ፡ በእርሱ አጸደቀች!

\+ \+ \+

## ልዑል እግዚአብሔር፡

ሃይማኖታችንና አገራችን፥ እናታችንና ንግሥታችን፡
እግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡
ከምድር ወደሰማያት የገባችበትን፡ የፍልሰቷን በዓል፡
ዘንድሮም፡ በ፳፻፯ተኛው (ኹለት ሽህ፡ ሰባተኛው) ዓመተ-ምሕረት፡
በያለንበት፡ በደኅና አድርሶ፡
እንኳን፡ በሰላም ለማክበር አበቃን!

\+ \+ \+

## ፍልሰታሃ ለማርያም!

## ድንግል ማርያም፡
## በመለኮታዊና ትስብእታዊ የተዋሕዶ ኹለንተናዋ፡
## ወደሰማያት የመውጣቷ ትንግርት!

**ሰማያዊ ልዕልና፡ ዘበዓለ ፍልሰታ ለማርያም።**

**ነሓሴ ፲፮ ቀን የሚከበረው፡**
**የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ወደሰማይ የመፍለሷ በዓል።**

[የግእዙ ቃል "መሢሕ"፡ በግሪክኛ፡ "ክርስቶስ" ይባላል።]

**"ፍልሰታሃ ለማርያም!"** በሚል ስያሜ፡ ነሓሴ ፲፮ ቀን የምትከበረው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የፍልሰቷ መታሰቢያ በዓለ ዕለት ዝክረ ነገር፡ እንዲህ ነው፡-

"ወልደ አብ ፡ ወልደ ማርያም"፡ "የአብ ልጅ ፡ የማርያም ልጅ" የኾነውና የተባለው፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ የመለኮትና የትስብእት ወላጆቹ ከኾኑት፡ ከእግዚአብሔር አብ አባቱ እና ከእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እናቱ፡ እንዲህ ተወልዶ፥ እርሷ፡ ቅድስት እናቱም፡ በመስቀሉ ሥር ሳይቀር በመቆም፡ ለአንዲት ቀን እንኳ ሳትለየው፡ ዲያብሎስንና የክፋት ሠራዊቱ የኾኑትን፡ ርኵሳን መናፍስቱንና ሰብኣውያን ግብረ ዐበሮቹን፡ በመሥዋዕትነትና በቤዛነት የፍቅር ኃይል፡ ከ፴፫ ዓመታት በላይ ለኾነ ዕድሜ በመዋጋት፡ በመጨረሻ፡ ኹሉንም፡ በድል አድራጊነት አሸንፎ፡ ከምድረ ገጽ አስወገደ።

ነፍሳዊዉንና ሥጋዊዉን፥ መንፈሳዊዉንም የድል አድራጊነት መሣሪያ፡ ለቅዱሳንና ለቅዱሳት ሓዋርያቱ፥ ላመኑበት ተከታዮቹም ኹሉ ካስረከባቸው በኋላ፡ ሕይወቱ በኾነው፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ ራሱ እስኪመለስ ድረስ፡ እርሷ፡ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመካከላቸው ባለችበት ጉባኤ ተሰባስበው ባሉበት፡ በዓይናቸው እያዩት፡ ወደሰማይ ዐረገ።

ባረገ፡ በዐሥረኛውም ቀን፡ አኹንም፡ እርሷ፡ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በእኒሁ ሓዋርያቱና ባመኑበት ተከታዮቹ መካከል ባለችበት ጉባኤ ተሰባስበው ሣሉ፡ **"አንትሙሰ ትጠመቁ፡ በመንፈስ ቅዱስ!"** ማለትም፡ **"እናንተ ግን፡ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ!"** ብሎ የሰጣቸውን፡ የተስፋ ቃሉን በመፈጸም፡ በኹሉም ላይ መንፈስ ቅዱስ ኾኖ ወረደባቸው፤ ተዋሓዳቸውም። (የሓዋ. ፩፥ ፬-፰። ፪፥ ፩-፬።)

ከዚህ በኋላ፡ እርሷ፡ ዋና ማእከላቸውና ሰብሳቢያቸው በመኾኗ፡ የእርሷና የእርሱ የኾነችውን፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትን ምሥራች፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ ለማዳረስ፡ እኒሁ ሓዋርያቱና ያመኑበት ተከታዮቹ፡ በየአህጉሩ ተበታተኑ። ተልእኳቸውን እየፈጸሙ ሲመለሱም፡ በእርሷ ዙሪያ እየተሰበሰቡ፡ ተልእኳቸውን ሲያስፋፉ፡ ለሠላሳ ዓመታት ያህል ዐብረዋት ኖሩ።

መቸም፡ አይሁድ፡ ኢትዮጵያዊው መሢሕ ኢየሱስ፡ በሥጋውና በደሙ የዋጃትና ዐትሞ ያጸናት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እየተስፋፋች የመኼዷን ትንግርት እያዩ፡ ዝም ብለው መቀጠልን፡ ሊቋቋሙትና ሊበግሩት የማይቻላቸው፡ የቍስል ላይ ቍስል ጦር ኾነባቸው። እንዲያውም፡ ይህ ኹኔታ፡ በእነርሱ ዘንድ፡ "አባታችን" በሚሉት፡ በአብርሃም ምክንያት፡ የቃል ኪዳን አምላካቸው የኾነውን፡ ቸሩ ፈጣሪያቸውን ካወቁበት ጊዜ አንሥተው፡ ከእርሱ ጋር፡ በክፋታቸው፡ ሲቋሰሉበት የኖሩትን፡ የልበ-ደንዳናነት ዓመፃቸውን፡ ጽኑ የቂም በቀል ነበልባላዊ እሳትን፡ በውስጣቸው ኮሰተረባቸው።

"ክርስቲያን ነኝ!" የሚለውን ወገን ጨምሮ፡ "ሃይማኖተኞች ነን!" እንደሚሉት፡ እንደዛሬዎቹ የዓለም ሕዝቦች ኹሉ፡ እነዚሁ አይሁድም፡ ለዚህ ሥጋታቸው፡ ማረጋገጫ፥ ደግሞም፡ ለህልውናቸው፡ ጠንቅ፥ ለሰላማቸው፡ የማሰናከያ ዐለትና ለመጥፋታቸውም ምክንያት ኾና የተጋረጠችባቸው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን፡ በቀናተኛው ዓይናቸው አስተውለው ተመለከቱ።

በዚህ ጊዜ፡ እርሷን ለማስወገድ የሚያመቻቸውን ዘዴ ሲፈልጉ፡ ቀደም ብለው፡ በተወዳጁ ልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተጠቀሙበት ግፍ፡ በቀላሉ፡ በቅርብ ተከሠተላቸው። ስለዚህ፡ አኹንም፡ ያንኑ ዘዴ፡ በእርሷ፡ በእናቲቱም ላይ ሊፈጽሙ ይዘጋጁ ጀመር።

ይህን ክፉ ዕቅዳቸውን፥ ደግሞም፡ እመ-እግዚአብሔር፡ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ በ፷፬ (ስድሳ አራት) ዓመቷ፡ ወደገነት የምትፈልስበት ጊዜ መድረሱን፡ አስቀድሞ ያወቀ መንፈስ ቅዱስ፡ ይህንኑ፡ እኩይ ውጥናቸውን፡ በሥራ ላይ ከማዋላቸው በፊት፡ በጥር ፳፩ ቀን፥ ፶፰ ዓመተ ምሕረት፡ በሕይወተ ሥጋዋ እንዳለች፡ ወደገነት እንድትነጠቅ አደረገ። ይህ፡ የመጀመሪያው ፍልሰቷ ነው።

የእግዚአብሔር እም፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ በሕይወተ ሥጋዋ እንዳለች፡ ወደገነት የመነጠቋ፡ ይኸው፡ መለኮታዊው ትንግርት፥ ማለትም፡ የፍልሰቷ ዜና መዋዕል፡ በሚቀጥለው፡ ንኡስ ርእስ ሥር፡ ተገልጾ ታገኙታላችሁና፡ ተመልከቱት!

## ሦስት ጊዜያት የኾነውና የተከሠተው፡

# የድንግል ማርያም፡ ትንግርታዊ ፍልሰት ዜና።

### "ፍልሰታ" ምንድር ነው?

"ፍልሰት"፥ ወይም፡ "ፍልሰታ" የሚባሉት አርእስት ቃላት፡ "ፈለሰ" ('ለ' ሳይጠብቅ) ከሚለው፡ "ከቦታ ወደቦታ መዘዋወርን"፡ ማለትም፡ "አንድ ሰው፡ ካለበት ቦታ ተነሥቶ፥ ወይም፡ መኖሪያውን ነቅሎ፡ ወደሌላ ተወሰደ!" የሚል ትርጒምን ከሚያመለክተው፡ ከግእዝ ዘር የተገኘ ዘይቤ ነው፤ ይኸው ቃል፡ በኢትዮጵያኛ፡ "ለ" ጠብቆ፡ "ፈለሰ" ያሰኛል።

ከዚህ የተነሣ፡ **የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሙሉ ሕያው ሰውነት፡ ከምድር፡ ወደሰማያዊቷ ገነት የመወሰዱን ተአምር ለማስረዳት፡"ፍልሰታ ለማርያም"** እንላለን።

ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ መነገር የጀመረው፡ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ተፈጽሞበት፡ እግዚአብሔር ወልድን ፀንሶ የወለደውንና ዐጥብቶ ያሳደገውን፡ ያን፡ የእግዚአብሔር እም፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ሕያው ሰውነት፡ አይሁድ፡ እጅግ በከፋው አላዋቂነታቸውና ሰይጣናዊ አስተሳሰባቸው፡ የሚቻላቸው መስሏቸው፡ በእሳት አቃጥለው ሊገድሏት በሞከሩበት ጊዜ ነው።

አዎን! ለእነርሱ መዳን ሲል፡ ለመሥዋዕትነትና ለቤዛነት፡ በሰውነት መጥቶ፡ ያን ተልእኮውን ፈጽሞ፡ ወደክብሩ በተመለሰው፡ በልጇ በወዳጇ፡ በኢየሱስ መሢሕ ሰውነት ላይ፡ አድርገውት የነበረውን፡ ያንኑ ግፍና ጭካኔያቸውን፡ አኹንም፡ በዚያ፡ በእርሷ መለኮታዊ ሰውነት ላይ ሊፈጽሙ ባሰቡበት፥ በማሰብ ብቻ ሳይወሰኑ፡ በሞከሩበትም ጊዜ ነው።

እነዚያ አይሁድ መስሏቸው እንጂ፡ እርሷንስ፡ እንኳን በእሳት ተቃጥሎ መሞት፡ አንዳችም ጉዳት፡ የጨረፍታ ያህል እንኳ ሊያልፍባት እንደማይታሰብ፡ አኹንም፡ ገና አላወቁም።

ገና ከመጀመሪያው፡ በፍጹም ሃይማኖቷና ምግባሯ፡ ሰውነቷን ለአምላክነት በማብቃቷ፡ እግዚአብሔር እም የተዋሓደቻትን፥ የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪት ኾና፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ አንድዩ ልጃቸውን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን፡ በመለኮትነትም፥ በሰውነትም ልትወልድለት የበቃችውን፡ የእርሷን፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ ሰውነት፡ እንዴት፡ ክፋትና ኃጢአት፥ ሞትና መቃብር፥ መበስበስና ሌላውም ዓይነት ሙስና፡ እንኳንስ ሊደርስበት፡ ሊቀርበውና ሊያስበውም እንኳ፡ አዎን! እንዴት ይቻለዋል? ፈጽሞ እንደማይቻለው፡ አዎን! ገና አላወቁም።

እንኳንስ እርሷ፡ ከላይ እንደተገለጠው፡ የእግዚአብሔር እም፥ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ መኾኗ የታወቀላት ቀርታ፡ በእርሷና በልጇ በማመናቸው፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" ተብለው፡ እየራሳቸውን፡ ለእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ያበቁት ኹሉ እንኳ፡ በእርሷና በልጇ መሥዋዕትነትና ቤዛነት ምክንያት፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋቸው እያሉም፡ ከክፋትና ከኃጢአት፥ ከሞትና ከመቃብር መበስበስ ሳይቀር፡ ነጻ ኾነው፡ ምንም ዓይነት ሙስናና ጉዳት በሌለበት፡ በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ዓለም፡ ቅድስቲቱን የትንሣኤ ሕይወት እንደሚኖሩ፡ አዎን! ገና አላወቁም።

በምድር ላይ፡ በትስብእትነት ተወጥኖ የተካኼደው፡ የእርሷ፡ መለኮታዊ ተልእኮ የተፈጸመው፡ እርሷን መስላ የተገኘች፡ ሰብአዊት ድንግልን በመዋሓድ፡ በዚያች ድንግል ማሕፀን፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ እግዚአብሔር ወልድን በመውለድ፡ "ብኪ ድኅነ ዓለም!" ማለትም፡ "ዓለም፡ በአንቺ ዳነ!" የተባለችበትን፥ ታላቁና የመጨረሻው፡ መለኮታዊ፥ ዘለዓለማዊና ሕያው ዓላማ የኾነውን፡ ፍጹም ድኅነትን [ፍጹም መዳንን] ማስገኘት መኾኑን፡ ገና አላወቁም።

አዎን! በምድር ላይ፡ በትስብእትነት ተወጥኖ የተካኼደው፡ የእርሱ የልጇ የወዳጇ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ መለኮታዊ ተልእኮ የተፈጸመው ደግሞ፡ መልካሙን ሰብአዊ ፍጥረተ-ዓለም፡ በክፋቱ ጠንቅ እያመሰ፡ ይኸው ሰብአዊው የፍጥረት ወገን፡ እርስ በእርሱ፡ ያለማቋረጥ በሚያካኺደው የጦርነት ዕልቂት፡ ሲጠፋፋ እንዲኖር በሚያደርገው፡ በዲያብሎስ ኃይል ላይ፡ ይኸው ልጇ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ በፍቅሩ ሥጋዊ መሥዋዕትነትና በምሕረቱ ደማዊት ቤዛነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ድልን በመጐናጸፍ፡ "ወበወልድኪ፡ ኮነ ሰላም!" ማለትም፡ "በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!" የተባለበትን፥ ታላቁና የመጨረሻው፡ መለኮታዊ፥ ዘለዓለማዊና ሕያው ዓላማ የኾነውን፡ ፍጹም ሰላምን ማስገኘት መኾኑን፡ ገና አላወቁም።

# የቅድስት ድንግል ማርያም

## የመጀመሪያው ፍልሰት።

"ፍልሰታ ለማርያም"ን በሚመለከት፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ዘንድ የኾነው ፍልሰታዋ የተፈጸመው፡ ከላይ፡ በዋናው ርእስ እንደተጠቀሰው፡ ሦስት ጊዜያት መኾኑን፡ አበክሮ ማወቅ ይገባል። ይህንም እውነታ፡ ከዚህ የሚከተለው፡ አጭር ዝክረ-ነገር ያስረዳል፦

አይሁድ፡ የሚቻላቸው መስሏቸው፡ ያን፡ የእግዚአብሔር እም፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን ሕያው ሰውነት፡ በእሳት አቃጥለው ሊገድሏት በሞከሩበት ጊዜ፡ እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ደግሞ፡ እነዚሁ አይሁድ፡ በእርሷ ሰውነት ላይ ሊያደርጉ ያሰቡትን፥ አስበውም አልቀረ፡ የቃጡትን፡ ያን ጉዳት ሊያደርሱ እንደማይቻላቸው፡ በመለኮታዊው ኃይሏ፡ እንዲሰማቸውና እንዲታወቃቸው አድርጋ፡ አሳየቻቸው። ይኸውም፡ እንዲህ ነው፦

ያ ጊዜ፡ ሓዋርያት፡ ከየሀገረ ስብከታቸው መጥተው፥ በእናታቸው ቅድስት ድንግል ማርያም ዙርያም ተሰባስበው፡ እንደተለመደው፡ ስለሓዋርያዊት ተልእኳቸው ሲነጋገሩ የሰነበቱበት ነው።

ወደየሀገረ ስብከታቸው ለመመለስ፡ ከመለያየታቸው በፊት፡ በኹለንተናዊ ደስታና ሓሴት ኾነው ለመሰነባበት፡ ሓዋርያት፡ እናታቸውን ቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ስለገናና ክብሯ፡ አጎበር ባለው መከዳ ላይ አስቀምጠውና ተሸክመው፡ እርሷና እነርሱም፡ ወዳስለመዷት፡ ወደጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ፡ ይዘዋት ሲኼዱ፡ አይሁድ አዩ።

ይህች ጌቴሴማኒ፡ ቀድሞ፡ ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሢሕ፡ የሚያዘወትራት፥ የመጨረሻዋን የሕማማት መስቀል ጽዋ ሞቱን የተቀበለባት፡ የዕለተ ዓርብ ዋዜማ በኾነችው፡ "ምሴተ ሓሙስ" በተባለችውም፡ የሓሙስ ምሽትና ማታ፡ እኒሁኑ ደቀ መዛሙርቱን ይዞ፡ ወደእርሷ ኼዶባት፡ ከእነርሱ ጋር የተሰነባበተባት፡ ያችው፡ ያትክልት ቦታ ናት።

አይሁድ፡ ይህ ዓይነቱ፡ የመንፈስ ቅዱስ ትዕይንት፡ ሲካኼድ ሲያዩ፡ ስለአምላክ እናት፡ ስለቅድስት ድንግል ማርያም፡ የታሰባቸው፡ ገናና ክብሯ ሳይኾን፡ ነዳይ ውርደቷ ኾነ! የታያቸውም፡ ሕያው ህልውናዋ ሳይኾን፡ የሥቃይ ሞቷ ኾነ! ከዚህ የተነሣ፡ ያ፡ በዝማሬ ድምፅ የተመላው የደስታ ዐጀብ፡ በዓመፅና በባዕድ አምልኮ ጨኸት ለደነቆረው፡ ለእነርሱ ጆሮ፡ ሙሾና የልቅሶ ዋይታ ኾነባቸው፤ በቅንዓት ጨለማ ለታወረው ዓይናቸውም፡ የቀብር ጉዞ ኾኖ ታያቸው፤ መቸም፡ እነርሱን፡ የሃይማኖት ክህደትና የምግባር ክፋት፡ መለያ ምልክቶቹ የኾኑለት፡ የፀረ-እግዚአብሔርነት ባሕርይ፡ አንዴ ተጠናውቷቸዋልና።

*እንዲህ፡ እንዲሰማቸውና እንዲታያቸው ያደረገው፡ ይኸው ሓሳዊና ምትሓታዊ ትዕይንታቸው፡ ለእነዚሁ አይሁድ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ነፍሷ፡ ከሥጋዋ ተለይታ፡ ማለትም፡ ["ላቲ ስብሓት!"] ሞታ፣ ሓዋርያት፡ ሊቀብሩዋት፡ ሬሳዋን፡ በአስከሬን ተሸክመው፡ ወደመካነ መቃብር የሚኼዱ አስመስሎ አቅርቦላቸው ኖሮአል። ስለዚህ፡ እንደልማዳቸው፡"እኒህ፡ የእነርሱ ተከታዮች፡ ቀድሞ፡ ልጇን፡ 'ተነሣ! ዐረገ!' እያሉ፡ ሲያውኩን ይኖራሉ፤ ዛሬ ደግሞ፡ እርሷን፡ 'ተነሣች! ዐረገች!' እያሉ፡ ሊያውኩን አይደለምን? ኑ! በእሳት እናቃጥላት!" ብለው ተነሡ። "ታውፋንያ" የሚባል አይሁዳዊ፡ ተራምዶ፡ እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የተቀመጠችበትን፡ የመከዳውን ሸንኰር ጨበጠው። ወዲያው፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ኹለቱንም እጆቹን ቀጣው። እጆቹም፡ በሸንኰሩ ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ።*

*ታውፋንያ፡ ሳያስበው፡ ድንገት በደረሰበት፡ በዚህ ጽኑ መቅሠፍት፡ እጅግ ተደናግጦ፡ እዚያው በወደቀበት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ! "የእውነተኛው የእግዚአብሔር ልጅ፡ የኢየሱስ መሢሕ እናት፡ በእውነት፡ አንቺ፡ ድንግል ማርያም ነሽ! ስለዚህ፡ እኔን፡ በደለኛውን፡ ይቅር ትዪኝ ዘንድ፡ እለምንሻለሁ!" ሲል፡ በልቅሶና በእንባ፡ ወደእናታቸው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ባቀረበው መማጠን፥ በሓዋርያትም ጸሎት፡ እጆቹ፡ ወደነበሩበት አካሉ ተመልሰውለት፡ ደኅና ኾነ! ምስጋናውንም፡ ከታላቅ ደስታ ጋር ገለጸ።*

*ከዚህ በኋላ፡ እርሷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመላእክት ተከልላና ተጠብቃ፥ በልዩ መለኮታዊ ይባቤ፡ ወደገነት ተነጥቃ ተወሰደች።*

*ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከምድር ወደሰማይ ያደረገችው፡ ያ፡ ቀዳማዊው የኹለንተና ፍልሰቷ የተፈጸመው፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ በጥር ፳፩ ቀን፥ በዕለተ እሑድ ነው። አዎን! ይህ፡ የመጀመሪያው ፍልሰቷ ነው።*

*እንግዴህ፡ ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ መነገር የጀመረው፡ አዎን! ይህ መለኮታዊ ትንግርት ከተፈጸመበት፡ ከፍልሰቷ ዕለት፡ ከጥር ፳፩ ቀን አንሥቶ መኾኑ ነው።*

*"መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ"፥ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" የምንላት፡ እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ እንዲህ፡ በመላእክት ታጅባ፡ በይባቤ፡ ወደገነት በተነጠቀችበት፥ ማለትም፡ በተወሰደችበት፡ በመጀመሪያው የፍልሰቷ ጊዜ፡ የኾነውን ደግሞ እንስማ!*

*ልጇ ወዳጇ ኢየሱስ መሢሕ፡ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ፡ ቅዱስ ሥጋውን እየቆራረሰና ክቡር ደሙንም እያፈሰሰ፡ የቤዛነቱን ተልእኮ እየፈጸመ ባለበት ሰዓት፡ ከመስቀሉና ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም አጠገብ ሳይለይ፡ የዚሁ ልጇን የአደራ ኑዛዜያዊ ቃል ተቀብሎ፡ እርሷን፡ እናት፥ ራሱንም፡ ልጇ አድርጎ፡ ይጠብቃት የነበረው፡ ወንጌላዊው ዮሓንስ፡ አኹንም፡ ዐብሯት ኾኖ፡ ይህንኑ የፍልሰቷን ምሥጢር ለማየት የበቃ ኾነ።*

ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡- ቅድስት እናታችንን፡ ማርያም ድንግልን፡ ቅዱሳን መላእክት፡ በደመና ነጥቀውና ዐጅበው፡ ከምድር ወደገነት በወሰዷት ጊዜ፡ ሓዋርያውንና ወንጌላዊውን ቅዱስ ዮሓንስን፡ ከብቅዓቱ የተነሣ፡ ዐብሩዋት እንዲገኝ አድርገውት ነበርና፡ በዕፀ ሕይወት [የሕይወት ዛፍ] ቦታዋ ማረፏን አይቶ፡ ወደምድር ተመለሰ።

ኋላ፡ በቀሩት ሓዋርያት መካከል ሣለ፡ እነርሱ፡ በጕጕት፡ ዙሪያውን ከብበው፡ "እናታችን፡ ድንግል ማርያም፡ እንደምን ኾነች?" ብለው ጠየቁት።

"እርሷ፡ እናታችን፡ ድንግል ማርያምማ፡ በገነት፡ በዕፀ ሕይወት ቦታዋ ዐርፋለች!" ብሎ መለሰላቸው።

*[ፍሬ ዕፀ-ሕይወትን፡ ማለትም፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ኢየሱስ መሢሕን ያስገኘችው፡ ድንግል ማርያም፡ ራሷ፡ ዕፀ-ሕይወት (የሕይወት ዛፍ) ስትኾን፡* "በገነት፡ በዕፀ ሕይወት ቦታዋ ዐርፋለች!" *የተባለበትን፡ እጅግ ጥልቅ የኾነውን፡ ይህን ምሥጢር፡ በአንክሮና በተመሥጦ እያስተዋሉ ይመለከቷል።]*

## ፊተኛው የሓዋርያት ሱባዔ ያስከተለው፡
## ኹለተኛው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰት።

የቀሩት ሓዋርያት፡ ይህን ታላቅ ተአምር ባለማየታቸው አዝነው፡ "ወንድማችን ዮሓንስ፡ ያን፡ የአንችን፡ በገነት፡ በዕፀ ሕይወት ቦታሽ፡ የማረፍሽን ዕፁብ ድንቅ እግዚአብሔራዊ ሥራ አይቶ፡ እኛስ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን!? አቤቱ፡ ይህን ቸርነትሽን፡ ለእኛም አድርጊልን!? ብለው፡ በጾምና በትሕርምት፥ በስግደትና በምጽዋት የታጀበ ጸሎታቸውን፡ ወደእናታቸው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በኅብረት ለማቅረብ አሰቡ፤ አስበውም አልቀሩ፡ ይህንኑ ለማድረግ፡ ተስማሙ።

ይህን፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ የኹለት ሳምንታት ትጋሀቸውን [ለጸሎት መንቃት]፡ እኒሁ ሓዋርያት፡ ዮሓንስን ጨምረው፡ በሱባዔ ሥርዓት፡ በሚቀጥለው የነሓሴ ወር መባቻ (መግቢያ)፡ እርሱም፡ በነሓሴ ፩ ቀን ጀመሩ።

ይኼም ሱባዔያቸው፡ የነገሩን ኹሉ፡ እውነተኛ ምሥጢር ስለገለጠላቸው፡ ፍሬያማውንና አማናዊዉን ምላሽ ማግኘት እንደቻሉ አረጋገጡ። እግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በዚህ፡ በኹለተኛው የሱባዔ ሳምንት ማብቂያ ዕለት፡ ይኸውም፡ በነሓሴ ፲፬ ቀን፡ እሑድ፡ በዚያው፡ በሕያዉ የሰውነት ኹለንተናዊ አካሏ፡ እንደገና፡ ወደምድር መጥታላቸዋለችና።

ሓዋርያት፡ በዚህ ሱባዔያቸው ያቀረቡት ጸሎታቸው፡ ካሰቡት በላይ፡ እንዲህ ኾኖ ተፈጽሞ በማግኘታቸው፡ እጅግ ደስ ብሏቸው፡ ለእርሷና ለፈጣሪያቸው፡ ታላቅ ምስጋናን አቀረቡ።

በልጇ ትንሣኤ ጊዜ እንደኾነውም፡ በመካከላቸው ተገኝታ፡ "ሰላም ለኵልክሙ!"፡ ማለትም፡ "ሰላም፡ ለእናንተ ይኹን!" አለቻቸው። ያም ኹኔታ፡ ለሓዋርያት፡ ያን፡ የአምላካቸውንና የጌታቸውን፥ የመምህራቸውንና የመድኃኒታቸውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ አስታወሳቸው። የእርሷንም፡ በዚህ፡ እውን በኾነው ሕያው ፍልሰቷ፡ ድንገት ተገልጣ፡ በመካከላቸው የመገኘቷን ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ እንደትንሣኤዋ አድርገው፡ በታላቅ ሓሤት ተቀበሉት።

እርሷም፡ ከዚያ አያይዛ፡ በብዙ የምሥራች ቃላት፡ እኒህኑ ሓዋርያትን አጽናናቻቸው። እነርሱም፡ በታላቅ ፍሥሓ ተመልተው፡ ከእርሷ ጋር፡ እስከነሓሴ ፲፮ ቀን ድረስ፡ ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት፡ ዐብረዋት ቆዩ። በዚያኑም የመጨረሻ ዕለት ተሠወረቻቸው።

የእርሷን፡ የእናታችውን፡ የድንግል ማርያምን፡ የፍልሰታዋን አስተርእዮ፡ "ከመ ትንሣኤ ወልዳ!"፥ ማለትም፡ "እንደልጇ ትንሣኤ!" ያሰኘው፡ ይህ፡ ከነሓሴ ፲፬ ቀን፡ እሑድ፡ እስከ ነሓሴ ፲፮ ቀን ማግሰኞ ድረስ ያለው የሦስት ቀኖች መዋዕል፡ በዚያው፡ በሕያዉ ሰብአዊ አካሏ፡ እንደገና፡ ወደምድር መጥታ የመገለጧና በመካከላቸው የመቆየቷ እውነታ ነው።

ከዚህ በኋላ፡ አልፎ አልፎ፡ በየግላቸውም ኾነ፡ በጋራ እየተገለጠችላቸው፡ ለአርባ ቀናት ያህል ዐብራቸው ሰነባበተች። እነዚህ፡ አርባ ቀኖችም፡ እርሷ፡ አኹን፡ ለእነርሱ የተገለጠችበት ኹናቴ፡ እንደልጇ ትንሣኤ ኾኖ መቅረቡን አምነው የተቀበሉባቸው ናቸው፤ ደግሞም፡ እርሷ ስላየቻቸውና ስላወቀቻቸው፡ ስለብዙዎች መለኮታውያት ምሥጢራት፡ ልታካፍላቸውና ልትገልጽላቸው የቻለችባቸው ናቸው፤ ይልቁንም፡ ልጇ፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ በዕለተ ዓርብ፡ ከመስቀለ ሞቱ በኋላ እንዳደረገው፣ እርሷም፡ ወደሲኦል ወርዳ፡ የፍልሰቷን ምሥራች፡ በዚያ ለነበሩት ነፍሳት የሰበከችባቸው ናቸው፤ እንዲሁም፡ በምድራዊው ዓለም ሣለች፡ ከቅድስት እናቷ ማሕፀን ጀምራ የኖረችባቸውንና የተዘዋወረችባቸውን፡ አኵስምን፥ ሊባኖስን፥ ቤተ ልሔምን፥ ናዝሬትንና ኢየሩሳሌምን፥ የገሊላን አውራጃዎች፥ የእስራኤልንና የይሁዳን፥ የዮርዳኖስንና የም ኣህጉር፥ ፍልስጥኤምን፥ ምድረ ከነዓንንና ግብፅን፥ ኢትዮጵያንና ሌሎቹንም መካናት በመጐብኘት፡ ውሱን ቆይታዋን ያሳለፈችባቸው ናቸው።

ይህን ኹለተኛውን ሕያው ፍልሰቷን፡ እንደልጇ ትንሣኤ አድርጋ እንደገለጠች ኹሉ፡ ሦስተኛ ፍልሰቷን ደግሞ፡ እንዲሁ፡ እንደልጇ ዕርገት አድርጋ ትገልጠው ዘንድ ፈቃዱ ስለኾነ፡ የሕያው ፍልሰታዋን እውነታ፡ ማሳየትና ማሳወቅ የጀመረችበትን፡ ነሓሴ ፲፬ ቀንንና የጨረሰችበትን፡ ነሓሴ ፲፮ ቀንን፡ እነዚህን፡ ሦስት መዓልታትና ሦስት ሌሊታት መነሻ በማድረግ፡ በአርባኛው ዕለት፡ በመስከረም ፳፩ ቀን፡ እንደልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወደሰማይ ዐረገች።

እንግዴህ፡ ይህ፡ "ፍልሰታ" የሚለው ዘይቤ፡ በጥር ፳፩ ቀን ተጀምሮ፡ በመስከረም ፳፩ ቀን ያበቃውን፡ የፍልሰቷን አስተርእዮ አካትቶ ለማዘከር ተብሎ፡ የተመደበ ቃል መኾኑን፡ በማስተዋል መመልከት ነው።

## ኋለኛው የሓዋርያት ሱባዔ ያስከተለው፡ ሦስተኛው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰት።

በልጇ፡ በወዳጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ብኵርናና ቀዳሚነት የተጀመረው፡ ያ፡ የመለኮት ምሥጢራዊ ትንግርት የኾነው፡ የትንሣኤና የዕርገት ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ እነሆ፡ አኹን ደግሞ በመጨረሻ፡ በእርሷ፡ በእናቲቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰትና ዕርገት፡ በበለጠ፡ ገሃድና እውን ኾኖ ታየ። ይህም ብቸኛ ታላቅ ተአምር፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች ተልእኮ አማካይነት፡ ይኸው፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ፡ በይፋ ተነገረ።

ይህን፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን፡ ተአምራዊ ፍልሰትና ዕርገት፡ በአንድ ጊዜ ለማየትና ምስክር ለመኾን የታደለው፡ የመጀመሪያው ሓዋርያ፡ ቅዱስ ቶማስ ብቻ ኾነ። የጌታችንን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ የትንሣኤውን ምሥራች፡ ከቀሩት ሓዋርያት ኹሉ ቀድማ ለማየትና ለመስማት፥ ለእነርሱም፡ አስቀድማ ለማሰማት፡ ማርያም መግደላዊት፡ የመጀመሪያዋ ሓዋሪት እንደኾነች ኹሉ ማለት ነው።

አዎን! እርሱ፡ ሓዋርያው ቶማስ፡ ቀድሞ፡ የልጇን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ የትንሣኤ ምሥራች፡ ከቀሩት ሓዋርያት ጋር ዐብሮ ለመስማትና ለማየት፡ ሳይታደል ቀርቶ የነበረ ሲኾን፡ አኹን ግን፡ ትንሣኤ ያላስፈለገውን፡ ይህን፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ የሕያው ህልውናዋ፡ ገሃድ አስተርእዮ፡ ማረጋገጫ የኾነውን ፍልሰቷን፥ እንዲሁም፡ የዚሁ ፍልሰታዋ አማናዊ መገለጫ የኾነውን ዕርገቷን ጭምር፡ በአንድነት፡ ለብቻው ለማየትና ለመስማት፡ ከቀሩት ሓዋርያት መካከል፡ ተለይቶ የታደለው፡ ይኸው፡ ሓዋርያው ቶማስ ኾኖ ተገኘ።

ከዚሁ፡ ከሓዋርያው ቶማስ ጋር የተያያዘው፡ የዚህ ርእስ፡ ዝክረ ነገር፡ እንዲህ የሚል ነው፡-

"ይህ ኹሉ ሲኾን፡ ማለትም፡ በመጀመሪያው ሱባዔ ጊዜ፡ ሓዋርያው ቶማስ፡ በቦታው አልነበረም። ለሓዋርያት በተሰጣቸው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል፡ እርሱም እንደለመደው፡ ደመና ጠቅሶ፡ እግዚአብሔር ባወቀውና ባደረገው ምክንያት፡ ዘግይቶ፡ በዚያ በደመናው እየተጓዘ፡ ከሀገረ ስብከቱ፡ ወደወንድሞቹ ሓዋርያት ሲመጣ፡ እግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እያረገች ሣለች፡ እርሷ በፈቀደችው በጎ መንገድ፡ ለእርሱ፡ ለቶማስ ተገለጠችለት።

"ያችም ዕለት፡ የእርሷ ፍልሰታዊ ትንሣኤ፡ እንደልጇ እንደኢየሱስ ክርስቶስ አማናዊ ትንሣኤ፡ ለሓዋርያት፡ በአስተርእዮ የተከሠቱባት፥ ከነሓሴ ፲፩ እስከ፲፮ ቀን ያሉትን፡ ሦስቱን መዓልታትና ሦስቱን ሌሊታት ያጠቃለለችውና መነሻ ያደረገችው፥ እንደልጇም ዕርገት፡ በአርባኛው ዕለት፡ ወደሰማይ ያረገችባት፡ መስከረም ፳፩ ቀን እሑድ ናት።

"በዚህ ጊዜ፡ ቶማስ፡ ከደመናው ሊወድቅ እስኪናወጽ ድረስ፡ ሰውነቱ ታውኮበት፡ 'ቀድሞ፡ ሌሎቹ ወንድሞቼ ሓዋርያት ኹሉ ታድለው፡ የልጅሽን ትንሣኤ ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ። አኹን ደግሞ፡ እነርሱ፡ ኹላቸው፡ ይኸው፡ የአንቺን ፍልሰት፡ ቀድመውኝ ሲያዩ፡ እኔ ብቻ ሳላይ ቀረሁ!' ብሎ፡ ማዘኑን ገለጠላት።

"ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ 'አይዞህ! አትዘን! እኒያ ወንድሞችህ፡ በልጄ ጊዜ፡ በመጀመሪያ፡ የእርሱን የትንሣኤ ምሥራች፡ ከሌሎች ሴቶች ሓዋርያት ሰምተው ሳያምኑ በመቅረታቸው፡ ኋላ፡ ከአንተ በፊት፡ እነርሱ ያዩት ቢኾንም፥ አንተ፡ ለጊዜው፡ በራስህ ፍላጎት፡ በዚያ ባለመኖርህ፡ ሳታየው ብትቀርም፡ ዕርገቱን፡ ዐብረሃቸው ኾነህ አይተሃል። አኹንም፡ እንደዚያኑ ጊዜ፡ እነርሱ፡ የእኔን፡ ፍልሰቴን ያዩ ኾነው፡ አንተ፡ ያላየህ ብትኾንም፡ ይኸው፡ አኹን ደግሞ፡ ዕርገቴን ያየህ፡ አንተ ብቻ እንጂ፡ እነርሱ አላዩም። ስለዚህ፡ ከእነርሱ ይልቅ፡ በበለጠ የታደልህ፡ አንተ ነህ፤ ፍልሰቴንም፤ ዕርገቴንም፡ ኹለቱንም፡ በአንድነት አይተሃልና!" ብላ አጽናናችው።

"ቀጥላም፡ እንዲህ አለችው፡- 'አኹንም፡ ወደእነርሱ ኼደህ፡ ‹ዐረገች!› ብለህ፡ የፍልሰታዬን ዕርገት ምሥራች ንገራቸው።' ይህንም ብላ፡ የውስጥ መጐናጸፊያዋን ሰጥታ፡ ሰደደችው። እርሱም፡ በግንባሩ ሰግዶና በእጇ ተባርኮ፡ በደስታና በምስጋና ዓይኖቹ እየተመለከታት ተሰናበታት።

"ቶማስ፡ ከቦታው ደርሶ፡ በሱባዔና በጉባኤ የሰነበቱ ወንድሞቹን ሓዋርያትን ሲገናኛቸው፡ 'ኧረ! የእናታችን ነገር፡ እንደምን ኾነ?" ብሎ ጠየቃቸው።

"እነርሱም፡ የኾነውን ትንግርት ኹሉ፡ ምንም ሳያስቀሩ፡ አንድ በአንድ እየተቀባበሉ ነገሩት።

"ቶማስም፡ ጸጥ ብሎ፡ ነገራቸውን አዳምጦ፡ ካስጨረሳቸው በኋላ፡ 'ታዲያ! አኹን፡ የት ነው፡ ያለችው? እጅግ ናፍቃኛለችና፡ ኼጄ፡ እንድሳለማት፤ እንድሰግድላትም፡ ያለችበትን ንገሩኝ!' አላቸው።

"በዚህ ጊዜ፡ ቅዱስ ጴጥሮስም፥ ዐብረውት ያሉት፡ የቀሩት ሓዋርያትም፡ ኹሉም፡ የሚመልሱት አጥተው፥ አቀርቅረው፡ ዝም አሉ።

"ቶማስም፡ ጥያቄውን በመቀጠል፡ 'እንዳወጋችሁልኝ፡ በትንሣኤ መልክ ከታየችበት፡ ከመጀመሪያው የፍልሰቷ አስተርእዮ በኋላ፡ እስካኹን እንዳስለመደቻችሁ፥ ልጇ ጌታችንም፡ እስከዕርገቱ ድረስ፡ ዐልፎ ዐልፎ እየተገለጠ ያነጋግረን እንደነበረው ኹሉ፡ ምናልባት፡ እርሷም፡ ድንገት፡ በመካከላችን፡ ትገኝ እንደኾነ፡ እንጠብቃት ይኾን?" አላቸው፤ እያንዳንዳቸውን፡ ተዘዋውሮ እየተመለከተ።

"እነርሱም፥ ኹሉም፡ 'አዎን! ልክ ነህ፤ ይህ ያልከው ነገር፡ 'አይኾንም!' አይባልም። ምናልባት፡ ሊኾን ይችላል!' በሚል ስሜት፡ ቀና ብለው እያዩት፡ ወደዝምታቸው ተመለሱ።

"በዚህን ጊዜ፡ ቶማስ፡ ባጭር ቃል፡ 'መቼም፡ ‹አታምኑኝም!› ብዬ ነው እንጂ፡ ደስ ይበላችሁ! እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፍልሰታዋ እንዳለች ኾና፡ ዐርጋለች! በልጇ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ ዕለት፡ በገዛ ድክመቴና ጥፋቴ፡ ከወንድሞቼ ሓዋርያት ጋር፡ ዐብሬ ባለመገኘቴ፡ በራሴ ላይ ያሳደርሁትን፡ የዘለዓለም የጸጸት እሳት፡ በርኅራኄዋና በቸርነቷ ልታስወግድልኝ ፈቃዷ ኾኖ፥ ለዚያ በደሌ፡ ዋጋዬን እኔ መክፈል ሲገባኝ፡ እንዲያውም፡ ‹ይህ ካሣ ይኹንህ!› ብላ፡ ይህን ቸርነት፡ ለእኔ፡ ለአገልጋይዋ አደረገችልኝ!' በማለት፡ ወንድሞቹ ሓዋርያት፡ ትኩር ብለው እየተመለከቱት፡ በግንባሩ ተደፍቶ፡ ሥቅሥቅ ብሎ አለቀሰ፤ የደስታ እንባውንም አፈሰሰ።

"እነርሱም፡ ባንድነት ኾነው፡ ከወደቀበት ካነሡት በኋላ፡ 'እንኳን ደስ አለህ!' ከሚል ቃል ጋር፡ እያቀፉ፡ በፍቅር አጽናኑት።

"ቶማስም፡ በደስታ ፈክቶ፡ 'እኔ በሌለሁበት ስለኾነው ኹሉ፡ እናንተ፡ አኹን ያላችሁኝን ጨምሮ፡ ከእርሷ ሰምቼዋለሁ። ለኹላችንም የሚኾን የእናትነት ምክሯንም ለግሣኛለች። በብዙ አጽናንታኛለች። ይህን የውስጥ ተደራቢ መጐናፀፊያዋን፡ ለኹላችንም፡ ለበረከት እንዲኾነን፡ ይኸውላችሁ፡ በእኔ እጅ ሰድዳላችኋለችና፡ እንካችሁ ተረከቡኝ!' ብሎ ሰጣቸው።

"ሓዋርያት፡ ያን፡ የእናትነት ስጦታዋን በማየታቸውና በማግኘታቸው፡ እጅግ ደስ ብሏቸው፡ በቅዱስ ጴጥሮስ አማካይነት ተቀብለው፡ ለበረከት ተካፈሉት።

"ይህ በኾነ፡ ልክ በዓመቱ፡ የቀሩት ሓዋርያት፡ 'ቶማስ፡ ፍልሰታዊ ዕርገትሽን አይቶ፡ እኛ ሳናይ፡ እንዴት እንቀራለን? እኛንም፡ ለዚህ ዕድል አብቅተሽ፡ እባክሽ አሳዪን!' ብለው፡ ወደፈጣሪያቸው የሚቀርብ፡ ኹለተኛውን፡ የ፪ ሳምንት ሱባዔያቸውን፡ ቶማስ ጭምር፡ ዐብሮአቸው በተሳተፈበት፡ በሚቀጥለው ነሓሴ ፩ ቀን፡ በተገቢው ጾምና ጸሎት፥ ትህርምትና ብሕትውና፡ በአንድነት ጀመሩ።

"የኹለተኛው ሳምንት ሱባዔ፡ በነሓሴ ፲፬ ቀን፡ እንደተፈጸመም፡ በነሓሴ ፲፭ ቀን፡ ሓዋርያት፡ በቅድሚያ፡ ከእየግል በአታቸው ወጥተው፡ በአንድነት በተሰበሰቡበት፡ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነቷና በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፥ በኪዳነ ምሕረትነቷም፡ ኹሉን አንድ አድርጋ የምትመለከውና የምታስመልከው፡ እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ተገልጣ፡ መለኮታዊ ክብሯንና ብርሃኗን ተጎናጽፋ፡ በመካከላቸው ተገኘችላቸው።

"በዚህ ጊዜ፡ እጅግ ደስ ብሏቸው፡ ወድቀው ከሰገዱላት በኋላ፡ ዙሪያዋን ኾነው፡ ሱባዔያቸውን፡ በሰላምና በፍቅር ስላስፈጸመቻቸው፥ በእርሱም፡ ተስፋ ያደረጉትን አማናዊ መልስ ስላስገኘችላቸው፡ ምስጋናቸውን፡ በኅብረት ጸሎታቸውና ዝማሬያቸው፥ ውዳሴያቸውና ቅዳሴያቸው አቀረቡ።

## በዓለ ፍልሰታሃ ለማርያም። [የማርያም፡ የፍልሰቷ በዓል።]

በመጨረሻ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፡ የሚከበረው፡ ታላቁ የፍልሰታዋ በዓል፡ እርሱን በሚመለከት፡ እስካኹን የተነገረውን ኹሉ፡ የሚያካትት ኾኖ፡ ፍጻሜው፡ በሰማያት ኾነ በምድር ዓለማት፥ በሥጋዊዉ ኾነ በመንፈሳዊው ፍጥረት ዘንድ፡ ምን እንደኾነ፥ ከምን ዓይነቱ የብቅዓት ደረጃም እንደደረሰ፡ አረጋግጦ የሚያሳየውን፥ በመለኮታዊውና በአማናዊው ዝግጅት የተፈጸመውን፡ ከዚህ የሚከተለውን፡ ሥርዓተ በዓል መመልከት ነው።

ይህንም እውነታ፡ እንዲህ የሚለው፡ አጭር ቃል ይገልጸዋል፡-

**በነሓሴ ፲፮ ቀን በሚውለው፡ በፍልሰታ ለማርያም በዓል ዕለት፡ ሓዋርያትና እነርሱን የመሰሉት ኹሉ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ወደሰማያዊቷ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ተነጥቀው ኼደው፡ እግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በመንበረ ጸባዖትነቷና በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያነቷ የምትገኝበትን ክብርና ምስጋና አዩ! ለዘለዓለምም፡ እያዩ ይኖራሉ።**

**ልጇ ኢየሱስ መሢሕ፡ እርሷን፡ ቅድስት እናቱን፡ መንበር፥ ራሱን፡ ሠራዒ (ዋና) ካህን፥ ሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስን፡ ንፍቅ (ረዳት) ካህን፥ ቀዳሜ ሰማዕት እስጢፋኖስን፡ ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ፡ ቀድሶ፥ ራሱም ቆርቦ፥ እናቱንም አቍርቦ፥ ካህናቱንና ሓዋርያትን፤ እነርሱን የመሰሉትንና በዚያ የታደሙትን አማኞቹን ኹሉ አቀረበ። ለዘለዓለምም፡ እያቀረበ ይኖራል።**

**በዚያን ጊዜ፡ በመላው ፍጥረታተ ዓለማት ዘንድ፡ በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም፡ ታላቅ ደስታ፥ ታላቅ ሓሤት ኾነ! ለዘለዓለምም፡ እየኾነ ይኖራል። (ራእ. ፲፩፥ ፲፱፤ ፲፪፥ ፩-፲፯።)**

## ማጠቃለያ እና መደምደሚያ።

"ፍልሰታ ለማርያም" በሚል ስያሜ፡ ነሓሴ ፲፮ ቀን ስለሚከበረው፥ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የሕያው ፍልሰታዋ መታሰቢያ ስለኾነው በዓለ ዕለት፡ እስከዚህ የተሰጠውን መልእክታዊ ሓተታ፡ ለማጠቃለልና ለመደምደም፡ ከዚህ የሚከተለው፡ ተጨማሪ ማብራሪያ፡ በጥቂቱም ቢኾን ቀርቧል፡-

በዘመነ ፍጥረት፡ "ዕፀ-ሕይወት" [የሕይወት ዛፍ]፥ በዘመነ ብሉይ፡ "ሓመረ-ኖኅ" [የኖኅ መርከብ]፥ በዘመነ ኦሪት፡ "ታቦተ-ሕጉ" [የትእዛዛቱ ማኖሪያ]፥ በዘመነ ሓዲስም፡ "ኪዳነ-ምሕረት" [የምሕረት ማኅተም] የተባሉት ስያሜዎች የተሰጧቸው፡ ግዙፋን አካላት እና ረቂቃን ባሕርያት፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ቀዳሚዎች አርአያዎቿ፥ ምሳሌዎቿና ጥላዎቿ መኾናቸው፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ተረጋግጦ ይታወቃል።

እንዲህ እንደመኾኗ፡ ለኹለንተናዊውና ለዘለዓለማዊው የመጨረሻው ትንሣኤ፡ በኵር ከኾነው፡ ከልጇ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቀጥላ፡ የእርሷ ብቻ በኾነው፡ በፍልሰትዋ የአዲስ ኪዳን ትንሣኤያዊ ሕያው አካሏ፡ ከምድር ወደሰማይ የመፍለስንና የማረግን ክብር ያገኘች መኾኗን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚሁ ሃይማኖታቸው ተቀብለው የሚኖሩበት እውነታ ነው።

እግዚአብሔር እም፡ ቀድማ በተዋሓደቻት፡ በዚያች፡ ሙሴ፡ ከእግዚአብሔር በተቀበላት ጽላተ ኪዳን ላይ፡ በራሱ፡ በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፈው፡ ራሱ እግዚአብሔር ቃል የተቀረጸባት ስትኾን፡ ያ የእግዚአብሔር ቃል፡ ጽላቷን፡ የራሱ አካል አድርጎ፡ በዘመነ ብሉይ፡ መለኮታዊ ክብሩን እንደገለጸባትና አምላካዊ ኃይሉን እንደፈጸመባት ይታወሳል፤ እንደዚያን ጊዜ ኹሉ፣ ኋላም፡ በዘመነ ሓዲስ፡ እግዚአብሔር እም፡ ቀድማ ከተዋሓደቻት፡ ከድንግል ማርያም፡ በዚያው ባሕርያዊ ጥበቡ፡ ከቅዱስ ሥጋዋ፡ ቅዱስ ሥጋን፥ ከቅድስት ነፍሷም፡ ቅድስት ነፍስን ነሥቶ፡ በተዋሕዶ በተገለጠበት የሰውነት አካሉና ባሕርዩ፡ ያን፡ በትንሣኤው፡ እውንና ገሃድ ያደረገውን፡ አማናዊዉንና ዘለዓለማዊዉን ክብሩንና ኃይሉን፡ አኹን ደግሞ፡ እርሷ፡ መለኮታዊትና ትስብእታዊት እናቱ፡ እነሆ፡ በፍልሰታዋ፡ ለፍጹምነት የልዕልና ማዕርጉ አበቃችው።

የዚህ አማናዊ እውነታ መነሻ፡ ድንግል ማርያም፡ "**ትፀንሲ!**" ማለትም፡ "**ትፀንሻለሽ!**" ያላትን፡ የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን፡ የምሥራች ቃል ተቀብላ፡ "**ይኵነኒ፡በከመ ትቤለኒ!**" ማለትም፡ "**እንዳልኸኝ (እንደቃልህ)፡ ይኹንልኝ!**" ባለችበት ቅጽበት፡ "**ቃል፡ ሥጋ ኮነ!**" ማለትም፡ "**አምላክ፡ ሰው ኾነ!**" በሚለው የሥጋዌ ምሥጢር፡ የተፈጸመ፡ ዕፁብ ድንቅ ትንግርት ነው።

የዚህ አማናዊ እውነታ መድረሻ ደግሞ፡ "**ወእምዝ፡ ተርኅወ መቅደሱ ለእግዚአብሔር፡ ዘውስተ ሰማይ፤ ወአስተርአየት ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር፡ እንተ ውስተ መቅደሱ።**" ማለትም፡ "**ከዚህ በኋላ፡ በሰማይ ያለው፡ የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፤ በመቅደሱ ያለችው፡ የኪዳኑ ታቦት ታየች።**" በሚለው፡ በዮሓንስ ራእይ ተረጋግጦ እንደተነገረው፡ በሙሴ አማካይነት፡ ለእስራኤል ተሰጥታ ቆይታ፡ ኋላ፡ ወደኢትዮጵያ ልጆች ተዛውራና በአደራ ተጠብቃ የኖረችው ታቦተ-ሕጉ፡ በኢየሱስ መሢሕ እና በድንግል ማርያም ሕያው ሰውነት፡ ወደሰማያት ተመልሳ በምትገኝበት ህልውናዋ የተገለጠው፡ ሌላው፡ ዕፁብ ድንቅ ተአምር ነው። (ሉቃ. ፩፥፴-፴፰። ዮሐ. ፩፥ ፲፬። ራእ. ፲፩፥ ፲፱፤ ፲፪፥ ፩-፲፰።)

ይህን ታላቅ ትንግርታዊ ኵነት [ኹነት]፡ እንዲህ በሚል ጥቂት ቃል፡ ልናቀርበው ይቻላል፤ ይኸውም፡-

በቅድሚያ፡ በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢርና ጥበብ፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን ላይ ዐርፎ የተፀነሰው፡ ያው፡ በጽላቷ ላይ ተቀርጾ የነበረው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑ፥

***ቀጥሎ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ቃል ስለተጻፈባት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የኾነችው፡ ጽላተ-ኪዳንና ይህችኑ፡ ጽላተ-ኪዳን በውስጧ በመያዟ፡ የድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነችው ታቦት [ሣጥን]፡ ኹለቱም፡ በምድር ላይ፡ ከነበሩበት ግዙፍ ህልውናቸው ተሠውረው፡ በሰውነት መገለጣቸው፥***

***በመጨረሻ፡ ኹለቱም፡ በሕይወተ-ሥጋ ኖረው፥ ተልእኳቸውንም ፈጽመው፡ ልጅዬው ኢየሱስ መሢሕ፡ በአዲሱ ኪዳን የትንሣኤ አካሉ፡ ከሙታን ተለይቶ በመነሣት፥ እናቲቱ ድንግል ማርያምም፡ ሙስና በማይነካው፡ በኹለንተናዊው የፍልሰት ሕያው አካሏ በመገለጥ፡ ኹለቱም፡ በዚያ ዘለዓለማዊ አካላቸው፡ ወደሰማይ ዐርገው፡ በፍጥረታተ-ዓለማቱ ዘንድ፡ ምንጊዜም ሰፍና እያለች፡ ነገር ግን፡ ለአብዛኛው ወገን፡ እስካኹን ድረስ፡ ተሠውራበት በኖረችው፥ በቅርቡ ግን፡ በይፋ ዐዋጅ በተከሠተችው፡ በዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታቸው ሰማያዊ ዙፋናቸው ላይ፡ እነሆ ዛሬ፡ ተቀምጠው የሚገኙ መኾናቸው ነው።***

***የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የሃይማኖትነቷና የመቅደስነቷ፥ የእናትነቷና የኪዳንነቷ፥ የአገርነቷና የንግሥትነቷ ፍቅር፡ በኢትዮጵያ ልጆቿ ዘንድ፡ እጅግ የጠለቀና የመጠቀ በመኾኑ፡ ቅዱሳንና ቅዱሳት ሓዋርያት፡ ለአምላክ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም፡ ባላቸው ተመሳሳይ ፍቅር፡ በጾም፥ በጸሎትና በምጽዋት [በበጎ ምግባር] ተጠምደው፡ ኹለት ጊዜያት ያካኼዱትን፡ ይህን፡ የኹለት ሳምንታት ሱባዔ፡ እኒሁ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚሁ መልኩ፡ በያመቱ፡ ለኹለት ሳምንታት፡ በሱባዔ ተወስነው የሚፈጽሙት፡ በዚህ ምክንያት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።***

***በጥር ፳፩ ቀን በኾነው፡ ምሥጠቷ [ወደሰማይ መነጠቋ] ተጀምሮ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን በኾነው አስተርእዮቷ የቀጠለውን፥ በመስከረም ፳፩ ቀን በኾነው ዕርገቷም ያበቃውን፡ ይህን የእናታቸውን፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን፡ የፍልሰታዋን ትንግርት፡ በፍልሰትዋ የሱባዔ ጾም ሰሞን፥ በተለይም፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፡ "በዓለ ፍልሰታ" ተብሎ በሚከበርበት ዕለት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እንደመላእክት፡ እንዲህ እያሉ በሚያሰሙት፡ የሌሊት ዝማሬ፡ ደስታቸው፡ የቱን ያህል የላቀና የመጠቀ፥ የጠለቀና የተመሠጠ መኾኑን ያመለክታል።***

***"ለፍልሰትኪ ከብካብ፡ ኀበ ዘሉዓሌ ተድባብ፤ እንዘ ይዌድሰኪ፡ ዘራማ ኪሩብ፤ ንግሥትየ፡ መርዓተ አብ።"***

***ማለትም፡ "አንቺ፡ የእግዚአብሔር አብ ሙሽራ፡ ንግሥቴ ሆይ! በራማ ያሉት፡ ሱራፌልና ኪሩቤል፡ ምስጋናቸውን፡ ለአንቺ ወደሚያቀርቡበት፥ አጎበሩ፡ ባለዘውድ ወደኾነው፥ ወደጽርሓ አርያም መንበርሽ፡ ያደረግሽው <u>ፍልሰትሽ</u>፡ በሰማያት የተፈጸመ የሠርግ በዓል ነው!"***

***ከዚህ የተነሣ፡ ይህንኑ፡ የፍልሰቷን በዓል፡ "ከመ ትንሣኤ ወልዳ" ማለትም፡ "እንደ ልጇ ትንሣኤ በዓል አድርገው ያክብሩት!" ሲሉ፡ የቀደሙት ወላጆቻቸው የደነገጉትን ተከትለው፡ እንደልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፡ በታላቅ ሓሤትና ይባቤ ያከብሩታል።***

እኒሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚህ፡ በቅድስት እናታቸው ድንግል ማርያም፡ የፍልሰታ በዓላቸው ዕለትና ወራት፡ የሚሰማቸው ፍሥሓ፡ በቃላት ሊገለጽ የማይቻለውን፡ በልጇ፡ በኢየሱስ መሚሕ የትንሣኤ በዓል ጊዜ፡ የሚሰማቸውን ስለሚመስል፡ ከነሓሴ ፲፮፡ እስከ ፴ ቀን ድረስ፡ ያሉትን ዕለታት የሚያሳልፏቸው፡ በፋሲካ ስሜትና ዝግጅት መኾኑ እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል።

ይህ የተመሥጦ ስሜታቸውና ዝግጅታቸው፡ ከሚገለጽባቸው፥ እግዚአብሔርም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በየልባቸው ከጻፋቸው፡ የማኅሌትና የመዝሙር በረከቶቻቸው መካከል፡ **"ንግሥተ ሰማያት ወምድር፡ ማርያም ድንግል! (፯ ጊዜያት) ኧኸ! ተፈጸመ ፍልሰታሃ! ተፈጸመ ፍልሰታሃ! ፍልሰታሃ ዘልዑል!"**

ማለትም፡ **"የሰማይና የምድር ንግሥት የኾነችው፡ የድንግል ማርያም፡ ፍልሰታዋ፥ እንደልዑሉ አምላክ ልጇ፡ እንደኢየሱስ መሚሕ ትንሣኤ፡ እውን ኾኖ ተፈጸመ!"** እያሉ የሚያቀርቡት የሽብሸባ ዝማሬ ይገኛል።

በመስከረም ፳፩ ቀን የሚውለውን፡ የፍልሰቷን ዕርገታዊ በዓሏንም፡ በዚሁ መልክ፡**"ንግሥተ ሰማያት ወምድር፡ ማርያም ድንግል! ኧኸ! ተፈጸመ ፍልሰታሃ! ተፈጸመ ፍልሰታሃ! ወዕርገታ ዘልዑል!"** ማለትም፡ **"የሰማይና የምድር ንግሥት የኾነችው፡ የድንግል ማርያም፡ ፍልሰታዋ፥ ዕርገቷም፡ እንደልዑሉ አምላክ ልጇ፡ እንደኢየሱስ መሚሕ ዕርገት፡ እውን ኾኖ ተፈጸመ!"** እያሉ በሚያቀርቡት የሽብሸባ ዝማሬ ያከብሩታል።

ደግሞም፡ እግዚአብሔር፡ ለሰብኣዊ ፍጡሩ፡ ዐቅዶ ያዘጋጀው፡ የቸርነት ሥራው፡ ለመጨረሻው ዘውድ የበቃ መኾኑ፡ በእርሷ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም የተረጋገጠበት፡ የዚህ፡ ዕፁብ ድንቅ ተአምሩ ዜና፡ በየጊዜያቱና በየቦታው፥ በየምክንያቱም፡ የሚነገር ከመኾኑ ጋር፡ እኒሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚያ በዓላቸው ጊዜ፡ **"ፈለሰት ውስተ አርያም፡ ማርያም ድንግል! በይባቤ መላእክት፡ ወፍጥረት፡ ዘልዑል!"** ማለትም፡ **"ገባች ወደአርያም፡ ማርያም ድንግል! በመላእክት፥ በፍጥረት፡ ምስጋና ለልዑል!"** የሚለውን የምሥራች ቃል፡ በታላቅ ሓሤት ይለዋወጣሉ።

ይህ፡ የደስታ መንፈስና ሥርዓት፡ የልጇ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የበዓለ-ትንሣኤው ወራት፡ የረቡዕና የዓርብ ጾም ሳይኖርበት፡ እስከበዓለ መንፈስ ቅዱስ ድረስ፡ ለአምሳ ቀናት ተራዝሞ፡ እንደሚከበር ኹሉ፡ የእርሷም፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ የፍልሰቷ በዓል፡ በእኒሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያኑና ኢትዮጵያውያቱ ዘንድ፡ በዚሁ መልክና ሥርዓት፡ እስከነሓሴ ፴ ቀን ድረስ መከበሩ ይቀጥላል።

እንግዴህ፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የአዲሱ ዓመት መግቢያና መነሻ ዐውደ ዓመት፥ የቅድስት ድንግል ማርያምና የልጇ የመድኃኒታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደታት፥ እንዲሁም፡ የኢትዮጵያ፡ የነጻነት በዓል ከኾነው፡ ከመስከረም ፩ ቀን በፊት፡ የዘመኑ፡ የመጨረሻ ታላቅ በዓላችን አድርገን፡ በየዓመቱ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፡ በያለንበት የምንዘክረውን፡ ይህን፡ የ"ፍልሰታ ለማርያም"ን በዓል፡ በምን ዓይነት የተመሥጦ ስሜት ልናከብረው እንደሚገባን፡ አስቀድመን ዐውቀነው፡ ልንዘጋጅበት ያስፈልገናል።

ለነሓሴ ፲፮ አጥቢያ ሌሊት፡ የምናካኺደው ሥርዓተ ቅዳሴ፡ ዮሓንስ፡ በራእዩ ያየውን፡ ያን፡ የሰማዩን ሥርዓት፡ በምድርም ላይ፡ እውን አድርገን፡ መፈጸማችን ነው። ይኸውም፡ ሊቀ ካህናታችንና ንጉሠ ነገሥታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ምድራዊትና ሰማያዊት መቅደሱ በኾነችው፡ በቅድስት ንግሥት እናቱ፡ በድንግል ማርያም ታቦትነትና መንበርነት ቀድሶ፡ ቅዱሳንና ቅዱሳት ሓዋርያቱን እንዳቆረበ፥ እንዲሁ፡ እኛም፡ በያለንበት፡ ዕለቲቱን በማዘከር፡ ምድራዊት መቅደሱ በኾነችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ቤተ ክርስቲያን ሰውነታችን፥ ቤታችንም፡ <u>ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የምንቀበልበትን፡</u> ያንኑ፡ ሰማያዊ የቅዳሴ ሥርዓት፡ መልሰን መፈጸማችን መኾኑን፡ ማመን ይገባናል።

\+ \+ \+

## <u>የበዓሉ ምንባቦች</u>

| | |
|---|---|
| የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት፡ ወደዕብራውያን፡ | ምዕ. ፲፥ ቁ. ፲፫-፳፫፤ |
| የዮሓንስ ራእይ፡ | ምዕ. ፲፩፥ ቁ. ፲፫-፲፱፤ |
| የሓዋርያት ሥራ፡ | ምዕ. ፩፥ ቁ. ፮-፲፬። |

**ወንጌል፡-** ሉቃስ ምዕ. ፩፥ ፴፱-፶፮።

**ምስባክ፡-** ወትቀውም ንግሥት በየማንከ፤
በአልባሰ ወርቅ፡ ዑጽፍት ወሁብርት፤
ስምዒ ወለትየ! ወርእዪ! ወአጽምዒ ዕዝነኪ።

ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች፤
የወርቅ ልብስን፡ በብርሃን ተጎናጽፋ፤
ልጄ ሆይ! ስሚ! እዪ! ጆሮሽንም አዘንብዪ!

**ዝማሬ፡-**

**ንግሥተ ሰማያት ወምድር፡ ማርያም ድንግል! (፪ ጊዜያት)**
**እኸ! ተፈጸመ ፍልሰታሃ! ተፈጸመ ፍልሰታሃ! ፍልሰታሃ ዘልዑል!**

<u>ትርጉም፡-</u>

**የሰማይና የምድር ንግሥት የኾነችው፡ የድንግል ማርያም፡ ፍልሰታዋ፥**
**እንደልዑሉ አምላክ ልጇ፡ እንደኢየሱስ መሢሕ ትንሣኤ፡ እውን ኾኖ ተፈጸመ!**

\+ \+ \+